# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 191 ጥር 3 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7 የትብብር ጥሪ ሲያደርግ ሁላችንም በአገር ማዳን ስሜት እንነሳ በሚል ብቻ አይደለም። የተለያዩ ርዕዮቶች እና አስተሳሰቦች ባላቸው ቡድኖች መካከልም ትብብር ሊኖር እንሚችል ግንቦት 7 ያምናል። በአንድ ድርጅት ውስጥ እንኳን የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቡድኖች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ጋር መተባበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

ግንቦት 7 ከዲሞክራሲና የነፃነት ኃይሎች ጋር መተባበር የሚፈልገው ዛሬ ተባብረን መታገላችን ለዘላቂው አብሮነታችን መሠረት ይጥላል ብሎ ስለሚያምን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በምእራብ ጎጃም ሁለት የወያኔ ሹሞች ሲገደሉ ሁለት ፖሊሶችና አንድ ሌላ ጄሌ መቁሰላቸው ተዘገበ

በአማራ ክልል ሥር በሚገኘው የምዕራብ ጎጃም ዞን በይልማና ዴንሳ ወረዳ በአዴት ከተማ በተነሳ የህዝብ ተቃውሞ ሁለት የወያኔ ሹሞች ሲገደሉ ሌሎች ሁለት ፖሊሶች እና ሌላ ጄሌ ባለስልጣን ከፉኛ መቁሰላቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ባለፈው ረቡዕ ጥር 2 ቀን ለወያኔ በጄሌነት አድረው ህዝባቸውንና አገራቸውን በመበደል ላይ የሚገኙት የወረዳው ባለስልጣናት የጨረቃ ቤቶችን ለማፍረስ በተንቀሳቀሱበት ጊዜ፣ ህዝቡ ቤታችንን አታፈርሱም በማለት አጥብቆ ተቃውሞ ነበር።

መለስ ዜናዊ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች በሃይል ለመተግበር እንዲያስችለው በየክልሉ አሰልጥኖ ባሰማራቸው አነጣጥሮ ተኳሾች የተማመኑ የወረዳው የወያኔ ጄሌ ባለስልጣናት ግን፤ ለህዝቡ ተቃውሞ የተለመደውን ንቀት በማሳየት ለተቃውሞ የተሰበሰበውን ህዝብ በፖልስ ሃይል ለማባረር በመወሰናቸው ውዝግቡ እየተካረረ ሂዶ ድንጋይ እስከመወራወር እንደደረሰ ተዘግቦአል።

የህዝብ ቁጣ ገንፍሎ ድንጋይ መወራወር መጀመሩ ይበልጥ ያበሳጫቸው የወረዳው ባለስልጣናት አጃቢ ፖልሶች ወደ ህዝብ መተኮስ በመጀመራቸው ከተሰብሳቢው ህዝብ አንዱ በያዘው ዱላ የአንድ ፖልሲ ጠመንጃ በመቀማት የወረዳውን ግብረሀይል ይመራ የነበረውን የወረዳው የኢንዱስትሪ ሀላፊ ይበሉ ደሴን ተኩሶ እንደገደለና አጠገቡ የነበረውን የከተማውን አፈ ጉባኤ እንድሪስን ክፉኛ አንዳቆሰለ ለማወቅ ተችሎአል።

የወያኔ አለቆቻቸው በከፈቱላቸው የሃብት ዘረፋና ሙስና ልባቸው ያበጠው የወረዳው ሹሞች የህዝቡን ተቃውሞ ከምንም ባለመቁጠር በገጠሙት ግብግብ ቤቱ እንዳይፈርስበት ለመከላከል በቆረጠው የአዴት ከተማ ነዋሪ ይህንን የመሰለ ቅጣት መቅመሳቸው መላውን ያካባቢውን ህዝብ እንጀት እንዳራሰና ወሬውም ወዲያው በመላው ወረዳና አካባቢው እንደተሰራጨ የግንቦት 7 ዘጋቢ አረጋግጦአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአወልያ ኮሌጅ ተማሪዎች የሚያደርጉትን አድማ እንደቀጠሉ ነው። በነቄምት ዩኒቨርሲት 2 ተማሪዎች መገደላቸው ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥን ኢሳት እንደዘገበው ከሳምንት በፊት የተጀመረው የአወሊያ ኮሌጅ ተማሪዎች ተቃውሞ እየከረረ በመሄዱ የወያኔ የጸጥታ ሀይሎች በተማሪዎች ላይ ስለሚወስዱት እርምጃ ግራ ተጋብተው የኮሌጁን ግቢ ዘግተው ተቀምጠዋል።

መንግሥት ተብዬው አገዛዝ ያሰማራቸው የኮሌጁ ባለሥልጣናት አለአግባብ የትምህርት ይዘቱን በመቀየራቸውና መምህራንን በማባረራቸው የተቆጡት የኮሌጁ ተማሪዎች ተቃውሞአቸውን ማሰማት ከጀመሩበት ያለፈው ማክሰኞ ጥር 1 ቀን ጀምረው ምግብ እንዳላገኙና ግቢያቸውን ለመልቀቅም ፈቃደኞች እንደልሆኑ የገለጸው ኢሳት የአወልያ ኮሌጅ እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በትናንትናው ዕለት ለተለያዩ የእስልምና ተከታዮች የስልክ ጥሪ በማድረግ ለዝሁር ጸሎት እንዲቀላቀሏቸው ጠይቀዋል ተብሎአል።

ኢሳት ተማሪዎቹን ለማግኘት በተደጋጋሚ ስልክ እንደደወለና የተደወለበት ስልኮች "ጥሪ አይቀበልም" የሚል መልስ ከማግኘት ውጭ ሊሳካለት እንዳልቻለ ገልጾአል።

ወያኔ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም ዘጎችየ በባህልና በቋንቋ ከመለያየት አልፎ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሙሲልም ሃይማኖትን ከክርስቲያን ጋር ለማጋጨት እንደሚንቀሳቀስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አንዱን ሙስሊም ከሌላው ለማጋጨት አክራሪ የሚል ታርጋ እየለጠፈ በአህባሽ እምነት አራማጆችና ዋህብይ ብሎ በሚጠራቸው ምዕመናን መካከል የጠብና የግጭት ግንብ እየገነባ መሆኑን ደጋግመን መዘገባችን ይታወሳል

ይህ በዚህ እንዳለ ሰሞኑን ለቀምት ከተማ በሚገኘው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ በሽብርተኝነት የ11 አመት እስር የተፈረደባቸው የስዊድን ጋዜጠኞች ጉዳይ አለም አቀፍ ትክረት መሳቡን ቀጥሎአል

ሥልጣንን በሃይል የሙጥኝ ብለው የአገራቸውን ሃብትና ንብረት ሲቦጠቡጡ በኖሩት የሰሜን አፍርካና የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች አምባገነን መሪዎች ላይ የደረሰው ህዝባዊ ቁጣ ያስደነበረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የመረጃ ፍሰትን ለመገደብ በሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች ላይ በደመ ነፍስ የወሰደ የድንጋጤ እርምጃ አገዛዙን በመላው አለም ይበልጥ እያጋለጠው እንደሚገኝ ጉዳዩን የተከታተለው የዝግጅት ክፍል ባልደረባችን ገለጸ።

በስዊድን አገር በሚታተሙ ታዋቂ ጋዜጦች፤ ሬዲዮኖችና ቴለቪዥኖች ላይ በተከታታይ እየወጡ ያሉ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት፤ በወያኔ እስር ቤት ታጉረው ያሉት ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነትና መረጃን የማግኘት መብቶች ያሉበትን አስከፊ ገጽታ አመላካች ናቸው ተብለዋል።

የም ዕራባዊያን ጋዜጦችና ፖለቲከኞች ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ላይ በተፈናጠጠበት የመጀመሪያዎቹ አመታት "አፍሪካን ለመለወጥ ብሩህ አዕምሮና ተስፋ ካላቸው ጥቂት መንግሥታት ተርታ የሚመደብ ነው" በማለት ሲያሞካሹት እንደነበር እየገለጹ ያሉት የስዊድን ጋዜጠኞች ፤ የመለስ ዜናዊ እውነተኛ ባህሪ የሆነው አምባገነንነትና ጨቋኝነት ከምርጫ 97 ጀምሮ እራሱን እየገለጸ መሆኑን በዜጎቹ ላይ እያደረሰ ያለውን አፈና፤ እሥራትና ግዲያዎችን በማስረጃ በማጣቀስ የሰላ ሂስና ትችት እያቀረቡበት ነው።

ህወሃት ያካሄድ በነበረው የጸረ ደርግ ትጥቅ ትግል ሌሎችን እያጋፈጠ ከግንባር ይሸሽ እንደነበር የቀድሞ የትግል ጓዶቹ የሰጡትን ምስክርነት እያጣቀሱ መለስ ዜናዊን ማብጠልጠል የጀመሩት የስዊድንና የሌሎች ስካንዲነቪያን ጋዜጠኞች፤ ዘጎቹን አፍኖ ለመግዛት የሚጠቀምበትን ር ህራሄ የሌለው የጭካኔ እርምጃውን በሁለቱ የአውሮፓ ዜጎቻቸው ላይ ወስዶአል በማለት ይከሳሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ እኛ መታሰር አለም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና የፕሬስ ነጻነት አፈና ለማወቅ ችሎአል ሲሉ በእስር ላይ የሚገኙት ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች መናገራቸውን ሲ ኤን ኤን ዘግቦአል።

ሲኤን ኤን የማርቲን ሺቢየ እናት የሆኑትን ካሪን ሽብየን አነጋግሮ እንደዘገበው ማርቲን ሽብየና ጆን ፔርሰን የአለም ህዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና የፕሬስ አፈና ለመረዳት በመቻሉ፣ ተልኮአቸው መና እንዳልቀረ ይረዳሉ ብሎአል።

"ጋዜጠኞቹ ንጹሀን ናቸው፣ ምንም ወንጀል እንዳልሰሩ ያምናሉ" ያሉት ካሪን፣ እስረኞቹ በኢትዮጵያ የፍርድ ሄደት ተስፋ የቆረጡ በመሆኑ ይግባኝ ላለማለት ወስናዋል በማለት ለሲ ኤን ኤን ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በአፋር ህዝብ ላይ እያደረሰ ላለው አፈናና ሰቆቃ ዋጋ ይከፍላል ሲል የአፋር ህዝብ ፓርቲ መግለጫ አወጣ

ወያኔ በአፋር ክልል እየፈጸመ ያለው አፈናና ሰቆቃ እየተባባሰ መሆኑን በመግለጽ ከትናንትና ወዲያ ማክሰኞ መግለጫ ያወጣው የአፋር ህዝብ ፓርቲ፤ አባቃላ እየተባለ በሚጠራው የማጎሪያ ካምፕ ውስጥ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ዘመዶች እና አገዛዙን የሚቃሙ አፋሮች በብዛት እየታጎሩ ነው ብሎአል።

ከ300 በላይ የሚሆኑት አፋሮች ላለፉት 2 አመታት ፍትህ አጥተው በእስር ላይ እንደሚገኙ ያተተው የፓርቲው መግለጫ፤ ዞን አንድ፣ ዞን ሁለትና ዞን ሶስት እየተባለ በሚጠራው አካባቢዎች አርብቶ አደሮችን እያፈናቀሉ መሬቱን ለአገዛዙ ሸሪኮች በኢነቨስትመንት ስም እየሰጡ መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህን ፖሊሲ የተቃወሙት ሁሉ ከስራቸው እየተባረሩና እየታሰሩ መሆናቸውን አጋልጦአል።

የአዋሽ ወንዝን ለተንዳሆ የሸንኮራ እርሻ ተክል በሚል አቅጣጫው እንዲቀየር በመደረጉ፣ የ ዱትባካሪ የሚገኙ ገበሬዎች በውሀ እጥረት ምክንያት የእርሻ መሬታቸውን እንዲተው ተገዷል ያለው የአፋር ህዝብ ፓርቲ መግለጫ፤ ናማሊፋን በሚባለው አካባቢ የሚገኙ የዶኮ ገበሬዎች የእርሻ መሬታቸውን ለቀሰም የሸንኮራ ተክል አስረክበዋል፤ አብዛኞቹ የአፋር ገበሬዎችም ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው በችግር ላይ ይገኛሉ ብሎአል።

መግለጫው በመቀጠልም የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ባቃዱ በተባለው አካባቢ የተለያዩ ጎሳዎችን እርስ በርስ የማጋጨት ተንኮል እየሰራ መሆኑንና በአፋርና ኢሳ ህዝቦች መካከልም ሆን ተብሎ ግጭቶች እየተቀሰቀሱ ለበርካታ ንጹሃን ህይወት ህልፈት ምክንያት እየሆኑ ነው ሲል አትቷል።

የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት የሆነው ኢስማኤል አሊሴሮ፣ እንዲሁም የክልሉ ባለስልጣናት የሆኑት ሙህመድ ከድር እና ስዩም አዋል (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## መደማመጥና መነጋገር ከቻልን የማንፈታቸው ልዩነቶች የሉም!!!

አገራችን እና ሕዝቧ በአንድ ጠባብ ዘረኛ ቡድን መዳፍ ውስጥ ናቸው። በአገራችን የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የግለሰብም ሆነ የቡድን መብቶቻቸው ተረግጠው በባርነት እየተገዙ፤ ጉልበታቸውና ሃብታቸው እየተመዘበረ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የምገኝ ዜጎችና ማኅበረሰቦች ሁሉ እጣ ፈንታችን ተሳስሯል። ሁላችንም ነፃ ካልወጣን በስተቀር ማናችንም በተናጠል የነፃነት አየር መተንፈስ አይቻለንም። ስለሆነም ለራሳችን የግልም የሆነ የቡድን ጥቅም ስንል እያንዳንዳችን ስለሁላችን ማሰብና መጨነቅ ግዴታችን ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሁሉም የዲሞክራሲና የነፃነት ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት የሚያደርገው ጥረት ፍሬ እያፈራ ቢሆንም አሁንም የንቅናቄዓችንን አቋም በትክክል ያልተገነዘቡ ወገኖች እንዳሉ እንገነዘባለን።

ስለሆነም በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያለንን አቋም ደጋግመን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

### 1. ሥልጣንን በተመለከተ

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሥልጣን ምንጭ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆን ይገባዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል። ሁሉም የአስተዳደር እርከኖች አንድ ዜጋ አንድ ድምጽ ኖሮት በሚካሄድ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የሚሾሙ መሆን ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ግንቦት 7፣ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማኅበረሰቦችና የተለያዩ እምነቶች ተከታዮች አገር መሆኗን ያውቃል። ለእንዲህ ዓይነቱ አገር ያልተማከለ ፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር የተሻለ ነው ብሎ ያምናል። በእያንዳንዱ ፌደራላዊ መንግሥት ውስጥም የዲሞክራሲ መሠረት የሆነው የአንድ ሰው አንድ ድምጽ መርህ መከበር አለበት ብሎ ያምናል።

ይህ መንገድ ነው በብዙሃን የሚደገፉ መሪዎችን ወደ ሥልጣን የሚያወጣልን።

### 2. መብቶችን በተመለከተ

ግንቦት 7፣ የግለሰብና የቡድን መብቶች መከበር ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

የቡድን መብቶችን ሰጥቶ የግለሰብ መብቶችን መንሳት ምንም አለመስጠት መሆኑ በተግባር ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ የምናየው ነው። መለስ ዜናዊ ለብሄር፣ ብሄረሰቦች የክልል መንግሥታዊ መዋቅርን፣ አርማን፣ መዝሙርን፤ በቋንቋ መማርና መዳኘትን እና የመሳሰሉትን መስጠቱ ዘወትር የሚነግረን ጉዳይ ነው። እነዚህ ሁሉ ዋጋ ያላቸው ነገሮች የሚሆኑት ከግለሰብ ነፃነት መከበር ሆነው ቢሆን ነበር። ሰው የሰውነት ብሎም የዜግነት መብቱ ካልተከበረ የቡድን መብቱ መከበሩ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ፍትህ ሳይኖር በቋንቋው መዳኙቱ ተበዳይን ምን ይጠቅመዋል? የመረጠውን ሰው መሾም፤ የማይስማማውን መሻር የማይችል ከሆነ በስሙ የሚጠራ መንግሥት መኖሩ ምን ይፈይድለታል?

በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 7፣ የግለሰብ መብቶች ብቻቸው በቂ ናቸው ብሎ አያምንም። እንደ ኢትዮጵያ ላለ ውስብስብ ታሪክ ላላት አገር የቡድን ፍላጎቶችና ስሜቶች በቸልታ ማለፍ አይቻልም። በግለሰብ ነፃነት ሥም የቡድን መብቶችን መደፍጠጥም ኢፍትሃዊ ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ሃይማኖቶች ጠንካራ የቡድን ስሜትና ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚችል ይገነዘባል።

በዚህም ምክንያት ግንቦት 7 ለሁለቱም የመብት ዓይነቶች እውቅና የሚሰጥ ድርጅት ነው።

### 3. ትብብርን በተመለከተ

ግንቦት 7 የትብብር ጥሪ ሲያደርግ ሁላችንም በአገር ማዳን ስሜት እንነሳ በሚል ብቻ አይደለም። የተለያዩ ርዕዮቶች እና አስተሳሰቦች ባላቸው ቡድኖች መካከልም ትብብር ሊኖር እንሚችል ግንቦት 7 ያምናል። በአንድ ድርጅት ውስጥ እንኳን የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቡድኖች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ጋር መተባበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

ግንቦት 7፣ የአንድ ወገን እውነት የሁሉም ወገን እውነት ላይሆን እንደሚችል ይገነዘባል። ለመደማመጥ ዝግጁዎች ከሆንን የጋራ ችግሮቻችን በርካታ ናቸውና በሚያስማሙን ጉዳዮች ላይ ተመርኩዘን ትግላችን ማጎልበት ይገባል ብሎ በጽኑ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ግንቦት 7 ከዲሞክራሲና የነፃነት ኃይሎች ጋር መተባበር የሚፈልገው ዛሬ ተባብረን መታገላችን ለዘላቂው አብሮነታችን መሠረት ይጥላል ብሎ ስለሚያምን ነው።

መደማመጥ፣ መሰማማትና መነጋገር ከቻልን የማንፈታቸው ልዩነቶች የሉም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

........................................................................................................................................................

## በምእራብ ጎጃም ሁለት የወያኔ ሹሞች ሲገደሉ ሁለት ፖሊሶችና . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ጀግናው የአዴት ከተማ ነዋሪ በገዛ አገሩ ከሰራው ቤት ሊያፈናቅሉት በተላኩት የወያኔ ጀሌዎች ላይ የተቀዳጀው ይህ ድል ለሌሎች ክልሎችና ከተማ ነዋሪዎች ታላቅ አርአያነት ሊኖረው የሚችል እንደሆነ የዘገበው ዘጋቢያችን ፤ ዱላ የያዘው የአዴት ነዋሪ በዱላው ዱላ ያልነበረው ደግሞ ከፊት ለፊቱ ባገኘው የድንጋይ ናዳ በወያኔ ተላላኪዎች ላይ ባደረሰው ጉዳት ከተገደሉት 2 ሹሞች በተጨማሪ ሁለት ፖልሶችና አብረዋቸው በነበሩ ሌሎች የወረዳው የወያኔ ጀሌዎች ላይ ቀላልና ከባድ የመቁሰል አደጋ እንዳደረሰባቸው ገልጾአል።

የገዛ ወገኖቻቸውን በማፈንና በማሰቃዬት የመለስ ዜናዊን የሥልጣን እድሜ ለማራዘም በሆዳቸው ተገዝተው ወያኔን እያገለገሉ ያሉ ፖሶች በወሰዱት የአጸፋ እርምጃም በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ድርሷል ተብሎአል። አብዛኞቹ ቁስለኞች በሞጣ ሆስፒታል ተወስደው እየታከሙ ሲሆን፣ ጉዳት የደረሰባቸው የወያኔ ተላላኪዎች እና ፖሊሶች ደግሞ ወደ ፈለገ ህይወት ሆስፒታል መወሰዳቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል።

በአዴት ከተማ ነዋሪዎችና በወያኔ ተላላኪዎች መካከል የተነሳውን ግጭት ለመቆጣጠር ግጭቱ በተነሳ በሰዓታት ጊዜ ውስጥ የፌደራል ፖሊስ ተልኮ አካባቢውን የተቆጣጠረ እንደሚገኝና ይህ ዜና እስከተጠናከረበት የዛረው ቀን ድረስ ውጥረቱ እንዳልረገበ ታውቆአል።

አካባቢውን በመቆጣጠር ላይ ያለው የፌደራል ፖሊስ መሳሪያ ቀምተው ባለሥልጣናቱን የገደሉትን ግለሰቦች በማደን ላይ ናቸው የሚለው ዘጋቢያችን ፖሊስ በርካታ ሰዎችን እንዳሰረም አረጋግጦአል። ከሟቾቹ አንዱ የሆነው ይበሉ ደሴ በቅርቡ ከጎንች ቆለላ ቀበሌ ወደ አዴት ከተማ ተዛውሮ የመጣ ሆድ አደር የወያኔ ጀሌ ነው ተብሎአል።

የአዴት ወረዳ ህዝብ በምርጫ 97 ወቅት ሙሉ በሙሉ ቅንጅትን የመረጠ እንደሆነ ይታወሳል።

## በአወልያ ኮሌጅ ተማሪዎች የሚያደርጉትን አድማ እንደቀጠሉ ነው። በነቁምት ዩኒቨርሲት 2 ተማሪዎች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የወለጋ ዩኒቨርስቲ ግጭት መፈጠሩን ተከትሎ ሲራጂ እና ከማል የተባሉ ሁለት የሕግ ተማሪዎች መገደላቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

ተማሪዎቹ የተገደሉት በፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት እስካሁን የተረጋገጠ ነገር ባይኖርም፤ ውስጥ አዋቂዎች "ተማሪዎቹ የሞቱት በምግብ መመረዝ ነው"ማለታቸውን ፍኖተ -ነፃነት የተባለው ጋዜጣ ዘግቧል።

የሟች ተማሪዎቹ የቀብር ሥነ ሥርዓት ባለፈው ማክሰኞ ጥር 1 ቀን ተፈጽሟል። ኢሳት ሰለጉዳዩ የዩኒቨርሲቲውን ሀላፊዎች ለማነጋገር በተደጋጋሚ ሞክሮ ፤ሀላፊዎቹ ስልካቸውን ለማንሳት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት እንዳልተሳካለት ገልጾአል።

አንድ ስሙ እንዲገለጽ ያልፈለገው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል፡- የሁለቱ ተማሪዎች መሞት ከምግብ መመረዝ ጋር የተያያዘ ነው በማለት ሁኔታውን ለማስተባበል እንደሞከሩ ገልጾ ተማሪዎቹ የሞቱት በምግብ መመረዝም ይሁን በግቢው ውስጥ ተነስቶ በነበረው ግጭት፤ አገዛዙን ከተጠያቂነት እንደማያድነው የህግ ባለሙያዎች አስተያዬታቸውን መስጠታቸውን ዘግቦአል።

ሰሞኑን በወለጋ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎችና በፌዴራል ፖሊሶች መካከል በተፈጠረ ግጭት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንደተቋረጠ ኢሳት መዘገቡንም አክሎ ገልጾአል።

## ወያኔ በአፋር ህዝብ ላይ እያደረሰ ላለው አፈናና ሰቆቃ ዋጋ ይከፍላል ሲል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የክልሉን መሬት ያለህዝብ ፈቃድ ለሶማሊያ ክልል አሳልፈው ለመስጠት ከወያኔ አለቆቻቸው ጋር እየዶለቱ መሆኑን የገጸው መግለጫ፤ ይህ እርምጃ ዋጋው የከፋ መስዋ ዕትነት ስለሚያስከፍል እንቅስቃሴው በአስቸኳይ ይቁም ብላአል።

የፓርቲው መግለጫው አያይዞም ወያኔ የአፋርን ባህላዊ አስተዳደር ለማንቋሸሽ ያለውን ፍላጎት በቅርቡ የአውሳ ሱልጣን በሚነግሱበት ጊዜ አሳይቷል ካለ በሁዋላ፣ የአናሳው መንግስት በክልሉ እየፈጸመ ላለው እኩይ ድርጊት ዋጋ ይከፍላል ሲል አስጠንቅቋል።

በመጨረሻም መላው የአፋር ህዝብ ለፍትህና ለዲሞክራስ እየተደረገ ያለውን ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪውን አቅርቦአል።

---



የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## ጠላት ጆሮው እየሰማ ዓይኑም እያየ ለክብራችን በአንድነት ጸንተን እንቆማለን!!!

ህወሃት ልዩነቶቻችንን አብዝቶና አርብቶ ክብራችንን አዋርዶ ረግጦ ሊገዛን ዘመኑን ሙሉ ሠርቷል። ለብዙ ግዜም አንዱን ህዝብ የአንዱ ጠላት አድርጎ ሲሰብክ ኑሯል። ይህንንም እውነት ለማስመሰል በበደኖ ፤በአርባ ጉጉ፤ በሃረርጌና በሌሎች ሥፍራዎች የብዙ ንጹሃን ዜጎችን ደም አፍስሶ ለርካሽ ፖለቲካ ፍጆታ አውሎታል። በደኖ ላይ አፈር ገፍቶ ይኖር የነበረ አማራ የተባለ ዘር የተጨፈጨፈው በህወሃት ፊታውራሪነት ነው። በአርባ ጉጉ ላይ የተፈጸመው አሰቃቂ ሰቆቃ አዛዥና አስፈጻሚው በመለስ ዜናዊ የሚመራው ህወሃት መሆኑን የምንዘነጋው ጉዳይ አይደለም። ልዩነታችን ውበታችን ሊሆን ሲገባው መጠቂያችን ሁኖ ጎድቶናል። በመለያየታችን ምክንያት ብዙሃኑ ለነጻነታቸው የሚያደርጉት ትግል ተዳከመ እንጂ አልጎለበተም። ጥቂቶች ብዙሃኑን ለመጨቆን አቅም አገኙ እንጂ አደብ አልገዙም። ተራርቀን በመቆማችን መለስ ዜናዊና ቡድኑ በክፍተቱ ተጠቀሙ እንጂ ነጻነት የተነፈገው ብዙሃኑ ያገኘው አንዳች በጎ ነገር የለም።

የመለስ ዜናዊና ቡድኑ ብርቱ ፍላጎት ኢትዮጵያዊያኖች የታሪክ እሰረኛ ሆነን ልዩነታችንን ማጥበብ ተስኖን ተከፋፍለን ተዳክመንና ተስፋ ቆርጠን እንድንኖር ነው። ይህን መፍቀድ ደግሞ ውረደት ነው።

በአገራችን ታሪክ ውስጥ በማወቅም ባለማወቅም ብዙ በጎ ያልሆኑ ነግሮች መፈጸማቸው እውነት ነው።ብዙሃኑ በጥቂቶች ተረግጠውና ተጨቁነው መከራቸው በዝቶ ዘመኑን ማሳለፋቸውም የሚካድ አይደለም።ጥንት ስህተት ተፈጽሟል። በዚህ ልዩነት የለንም። ብዙዎቻችን እንስማማለን።ልዩነታችን የሚሰፋው ያን ክፉ ስህተት መልሰን እንደግመዋለን በሚሉና ከስህተቱ ተምረን አንዲት ጠናካራ አገርን እንመስርት በሚባልበት ግዜ ነው።

ግንቦት ሰባት ጥንት የተፈጸሙ ክፉ ነገሮችን ለመደግም ፍላጎት የለውም።ያ ስህተት እንዳይደገም በርትቶ የሚሰራ ንቅናቄ ነው።ከጥንቱ ስህተት ልምድ ቀስመን ያን ስህተት ላንደግመው ቃል ገብተንና አብረን ለመታገል ቆርጠን ቆመናል። ከስልጡን ዜጋና ለመጪው ትውልድ ኃላፊነት ከሚሰማው ዜጋም የሚጠበቀው ይሄው ነው እንጂ ጥንት የተፈጸመውን እያመነዥኩ በጥላቻ ሰንሰለት ታስሮ ነጻነት እቀዳጃለሁ ማለት አይደለም።ጥንት እንዲህ ሆነናልና ዛሬ አብረን አንቆምም ማለት መለስ ዜናዊ የቆመለትን ዓላማ ከማስፈጸም ውጪ መከራውና ስቃዩ በዝቶበት ለሚኖረው ህዝባችን የሚፈይደው ከቶ ምን ይሆን?

እንደ ግንቦት ሰባት እምነት የታሪክ እሰረኛ ሁነን በጎ ነገር ሳንሰራ የምንቀረውም ከወደፊቱ ይልቅ የትናንቱን የታሪክ እንከኖች እያቦካን መኖርን ስንመርጥ ነው።የህወሃትም ህልምና ምኞትም የታሪክ እሰረኛ ሁነንና ተዳክመን እንድንኖር ነው እንጂ በአንድነት ቆመን ነጻነታችንና ክብራችንን እንድናስጠብቅ አይደለም። ከመቶ ዓመትና ከዚያ በፊት የተፈጸሙ ክፉ ነገሮች ለነገው ነጻነታችን እንቅፋት ሁነው እንዲቆሙ ማድረግ ነጻነቴን እፈልጋለሁ ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም። ያለፈውን እያሰቡ የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ማጨለም ነቀፌታ በተለባሰው ታሪክ ውስጥ ራስን እሰረኛ ማድረግ ነው። ነጻነቱን የሚፈልግ አስቀድሞ ከዚህ እስራት ራሱን ማስፈታት አለበት። ከዚህ እስራት ያልተፈታ የነጻነትን ጣእም አያውቃትምና ሌላውን ነጻ ሊያወጣ የሚችል የሞራል ብቃት ይኖረዋል ለማለት አይቻልም።

ግንቦት 7 ከእንዲህ ዓይነቱ እስራት የወጡ ዜጎች ስብስብ ነው። በዚህም ምክንያት ለነጻነታችንና ለክብራችን ስንል ጠላት ዓይኑ እያየ ጆሮውም እየሰማ ግንባራችንን ሳናጥፍ በአንድነት ጸንተን ጠላቶቻችንን ከመታገል ውጪ የቀረን ምንም ምርጫ የለንም ብሎ ያምናል። መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ጠላቶቻችን ናቸው። ነጻነታችንን ነፍገው ክብራችንን አዋርደውና ረግጠው ሊገዙን የሚሞክሩ ኃይሎች ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው። የአገራችንን ድንበር አፍርሰው ዜጎችን አፈናቅለው ለም መሬቶቻችንን ለባእዳን የሚሰጡ ወይም ለራሳቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉ ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው።ዜጎች በነጻነት እንዳያስቡ የዜጎችን የማወቅ መብትና ነጻነት የሚገደቡ ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው። ንጹሃን ዜጎችን በሃሰት ከሰው በሃሰት አስፈርደው ለስቃይ የሚዳርጉ በሙሉ ጠላቶቻችን ናቸው። የአገሪቷን ወጣቶች ከአገራቸው መሰደድና በየበረሃው ቀልጠው እንዲቀሩ ምክንያት የሆኑ ኃይሎች በሙሉ ጠላቶቻችን ናቸው። ይህን የመሰለ ህያው ጠላት እያለን ከሙታን ጋር ውጊያ ውስጥ መግባት ጅልነት ካልሆነ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? የዛሬውን ህያው ጠላት ህወሃትን በአንድነት ሁኖ ለመታገል እምቢ ማለትስ የነጻነትን ትርጉም አለማወቅ ካልሆነ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ግንቦት ሰባት የነጻነት፤ የዴሞክራሲና የፍትህ ንቅናቄ ከትላንትናው በደል ይልቅ የዛሬው በደል ያንገበግበዋል። ከጥንቱ ጉድፍ ይልቅ የመጪው ትውልድ እጣ ፈንታ ያስጨንቀዋል። የዛሬው በደል ያንገበገባቸው ኢትዮጵያዊያን ስጋና አጥንታቸውን ከመቁጥር አልፈው ከአራቱም አቅጣጫ ተጠራርተው በአገራችን ውስጥ ፍትህ ነግሶ፤ ነጻነት ሰፍኖ፤ ህዝቦቿ በሠላም በፍቅርና በአንድነት እንዲኖሩ ለማየት ብርቱ ፍላጎት ባላቸው ወንዶችና ሴቶች የተቋቋመ ንቅናቄ ነው። የግንቦት ሰባት ጠላቱ የዛሬው ህወሃት እንጂ የትላንትናዎቹ ፊውዳሎች ወይም ደርጎች አይደሉም። እነርሱ ዛሬ የሉም። ጠላታችን በእነርሱ መቃብር ላይ የቆመው ዘረኛውና ዘራፊው ህወሃት እንጂ በዛሬውና ነጌው ህይወታችን ላይ ቅንጣት ታክል ተጽዕኖ መፍጠር የማይችሉ የትናትናዎቹ ሙታኖች አይደሉም።

ህወሃትን የመሰለ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን በራሳችን ላይ ተጭኖ እርሱን በአንድነት ሆነን ከመታገል ፈንታ "እንዲያና እንዲህ" ሁነን ነበር እያሉ ማላዘን ጥቅም የለውም። ጥቅም አለው ከተባለም የሚጠቅመው ህወሃትን እንጂ ነጻነቱን ተነፍጎ የኖረውን ህዝብ አይደለም። ነጻነትን ለመቀዳጀት የፈለገ እርሱ የጠላት ጆሮ እየሰማ አይኑም እያየ እጅ ለእጅ ተያይዞ ጠላትን ለመፋለም መዘጋጀት አለበት። አዎን አማራጫችን አንድ ሆነን ህያው የሆነውን ጠላታችንን መታገል ነው። አንድ ሆነን አንታገለም ማለት ጠላት ህዝባችንን እስከ ልጅ ልጆቻችን እንደጨቆነ ይዝለቅ ከማለት ውጪ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም።

ህያዊያን ጠላቶቻችንን በጋራ ለመዋጋት ከልብ የምናቀርበውን ጥሪ የሚጠራጠሩና ከሙታኖች ጋር የገጠሙት ጦርነት ያልበረደላቸው ወገኖቻችን ሊያውቁት የሚገባው አንድ ቁምነገር ቢኖር፤ ግንቦት ሰባት ምንም የተደበቀ አጀንዳ የሌለው መሆኑን ነው። የንቅንቄያችን አጀንዳ ለሰው ሁሉ የተገለጸ እንጂ የተሰወረ አይደለም። አጀንዳችን ነጻነት፤ ፍትህ፤ እኩልነት እና ዴሞክራሲ የሰፈነባት አገር ተገንብታ ማየት ነው። ይህንን ለማስፈን አሉ የሚባሉ መንገዶችን ሁሉ እንጠቀማለን። ከሁሉም ነጻነት ፈላጊ ኢትዮጵያዊያን ጋር አብረን እንሰራለን።ሊረዱን የሚፈልጉ ወዳጆችን ርዳታ ሁሉ እንደአስፈላጊነቱ እንጠቀማለን። ይህን ሁሉ የምናደርገው ለስልጣን አለመሆኑን አሁንም ደግመን ደጋግመን እንናገራለን። የምንታገለው አገራችንን ከጥፋት ማዳንና በዚያችም አገር ውስጥ ስልጣን ላይ የሚወጣበትን ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍጠር ነው። ይህንን ደግሞ ጠላት ዓይኑ እያየ ጆሮውም እየሰማ እናደርገዋለን።

**ድል ለነጻነት ታጋዮች በሙሉ !!!!**

## አሸባሪው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ -ክርስቲያን ህንፃዎች ህገ-ወጥ ናቸው በማለት ማፍረሱ ተቃውሞን

ለበርካታ አመታት በተለያዩ ጊዚያቶች ሆን ብሎ የንግድ ቦታዎችን በማቃጠል ነዋሪዎችን ሲያፈናቅልና ለችግር ሲዳርግ የቆየው አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ ፊቱን ወደሃይማኖት ተቋአማት በማዞር ሰሞኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ -ክርስቲያን ህንፃዎች ህገ-ወጥ ናቸው በማለት ማፍረሱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በማን አለብኝነት እንዲፈርሱ ከታዘዙት ህንጻዎች ውስጥ ዳግማዊ ምኒልክ ፊት ለፊት በሚገኘው በተለምዶ «ጠጠር ሕንፃ» በሚባለው ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያኑአ ግንባታዎች ሲሆኑ ሕገወጥ እየተባሉ እንዲፈርሱ መደረጋቸው ከፍተኛ ተቃውሞ ማስነሳቱ ተይይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

በተመሳሳይ መልኩ የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ አስተዳደር መሰንበቻውን በቤተክህነት ሕንፃ ላይ ባካሄደው ዘመቻ፤ አምስት የንግድ ቤቶችንና መጋዘኖችንማፍርሱን የዘገበው ሪፖርተራችን ፤ ከቤተክህነት ቤቶቹንና መጋዘኖቹን ተከራይተው ይሠሩ የነበሩ ነጋዴዎች የጥቃቱ ሰለባ መሆናቸው ታውቁአል። ግለሰቦቹ የአሸባሪው አገዛዝ የወረዳ ባለስልጣናት የወሰዱት ዕርምጃ ሕጋዊነት የሌለው ነው በማለትም ተቃውሞአቸውን በማሰማት ላይ ይገኛሉ።

አጥፊው የወያኔ አገዛዝ በተለይም ለአማራው ህዝብ ካለው ስር የሰደደ ጥላቻ በመነጨ ስሜት በምርጫ 97 ወቅት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያንን፡-"የነፍጠኞች መሸሸጊያ ዋሻ ሆኗል " በማለት የማስፈራሪያ ዛቻ ሲነዛ እንደነበር ይታወቃል።

ሽብርተኛው የወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠረ ዜጎችን የማፈናቀል ተግባሩን እንደ አንድ የፓሊሲ አካል አድርጎ መንቀሳቀስ የጀመረው ከረጂም አመታት በፊት ጀምሮ ሲሆን ቁልፍ የገቢያ ቦታዎችን ከወያኔ ጋር ሽርክና ላላቸው ለዘመኑ ከበርቴዎች በመሸጥ ሃብት ለማካበት በሚደረግ ጥድፊያ በቅርቡ በዴሴና በአድስ አበባ ከተማ የተለያዩ የመገበያያ ቦታዎች በእሳት እንዲጋዩ መደረጉ መዘገቡ ይታወሳል። በአዋሬ ገበያ ላይ ታህሳስ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ዕኩለ ሌሊት ሆን ተብሎ በተቀሰቀሰ ቃጠሎ ከ80 ያላነሱ የንግድ ሱቆችና መኖርያ ቤቶች እንዲሁም በሚሊየኖች የሚገመት ንብረት እንዲወድም መደረጉ አይዘነጋም፡፡ የንግድ ቤቶችና መኖሪያዎች መውደማቸውን ተከትሎ፣ በአካባቢው ኗሪ የነበሩ ሰዎች ጐዳና መውደቃቸውና ሕገወጥ ናችሁ በመባል ጊዜያዊ መጠለያ እንዳያገኙ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

አረመኔው አገዛዝ ለነኘህ ሜዳ ላይ ለወደቁ ዜጎች ቀይ መስቀል ድንኳን ለመስጠት ያደረገውንም ሙከራ በጭካኔ ማገዱ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

## በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ የወሰደው እርምጃ፣ የሚደነቅ ነው ሲሉ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ መናገራቸው ተዘገበ

የቀድሞው የኦሮሞ ፌደራሊስት መስራችና ሊቀመንበር እንዲሁም አሁን የንቅናቄው የክብር ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በጄኔራል ከማል ገልቹ የተመራው ኦነግ የወሰደው እርምጃ የኦሮሞ ህዝብ ያለበትን ስቃይና መከራ ለመቅረፍ ወደፊት አንድ እርምጃ የሚያስከድ ነው በማለት እንደሚያደንቁት መናገራቸውን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት ከአቶ ቡልቻ ደመቂሳ ጋር ባካሄደው ቃለ መጠይቅ "የኦሮሞ ህዝብ የሚሸሽ ወይም የሚገነጠል ህዝብ አይደለም" ማለታቸውን ጠቅሶ ሁሉም በዚህ ሀሳብ ዙሪያ ቢሰባሰብ ጤነኛ እንሆናለን የሚል የጸና እምነት እንዳላቸው መናገራቸውን በድምጽ አስምቶአል።

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ሃይል በኦሮሞና በተቀሩት ህዝቦች ላይ እያደረሰ ያለው የመብት ረገጣ ከምንግዜውም የከፋ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ቡልቻ የጄኔራል ከማል ቡድን ከዚህ በፊት ሌላ አይነት ፕሮፓጋንዳ ሲመገብ ያደገውን ወጣት ኦሮሞ ለመቀየር ከባድ ፈተና እንደሚጠብቀው መግለጻቸውን ዘግቦአል።

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ የወሰደው የፖለቲካ አቋም ለውጥ ለፍትህ፤ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲ በሚታገሉ ሃይሎች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት እየተቸረው ያለ ቢሆንም በሌላ በኩል ያለው የኦነግ ቡድን የኦሮሞን ህዝብና የተቀረውንም የኢትዮጵያዊ ህዝብ እኩል ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችለውን የ ዲሞክራሲ ሥር ዓት በአገራችን በማስፈን ኢፍትሃዊነት ያስከተለውን መብት ረገጣ፤ ድህነትና ጉስቁልና ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ለማሽቀንጠር የሚደረገውን የጋራ ትግል እንዲቀላቀል ጥሪ እየቀረበለት ይገኛል።

## በጋምቤላ ክልል በአኙዋኮች ላይ ለተፈጸመው ዕልቂት ተጠያቂ ከሆኑኩ መሳሪያና ወታደር የሰጠኝ መለስ ዜናዊም እኩል ተጠያቂ ይሆናል ሲል የጋምቤላ ርዕሰ መስተዳድር ፕሬዝደንት መግለጹ ተዘገበ

የህወሃት ታማኝ አገልጋይ በመሆኑ ለጋምቤላ ክልል ፕሬዝዳንትነት ሥልጣን የበቃው ኦሞት ኦባንግ አሎም ከ8 አመት በፊት በጋምቤላ ለተፈጸመው የአኝዋኮች ጭፍጨፋ በሃላፊነት ተጠያቂ ሆኘ "እኔ ከታሰርኩ መለስም ይታሰራል" በማለት በከፍተኛ የፌደራል ባለስልጣናት ፊት መናገሩን soldiarity movemnet for new Ethiopia ወይም በአማሪኛ አጠራሩ ለአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የተባለው ድርጅት ድህረገጽ ላይ የወጣ ዘገባ አስታወቀ።

በክልሉ ነዋሪዎች "እውነተኛው ወያኔ" የሚል ስያሜ የተሰጠው ኦሞት ኦባንግ ይህንን የተናገረው ከታህሳስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ፌደራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚመራ ቡድን በአኝዋክ ንፁሃን ላይ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ ግምገማ በጀመሩበት ወቅት "የሚገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር አዘጋጅተህ አቅርበሃል" የሚል ውንጀላ ሲያቀርቡበት በሰጠው ምላሽ እንደሆነ ዘገባው አመልክቶአል።

በድህረ ገጹ ዘገባ መሠረት በግምገማው ላይ የተሳተፉ ታማኝ ምንጮች እንዳስታወቁት በክልሉ በሙስና ተዘርፏል በተባለ 80 ሚሊዮን የሚጠጋ ገንዘብ፣ በብቃት ማነስ፣ ልማትን በማጓተትና በጎሳዎች ዕርስ በርስ ግጭት ሰበብ እየተካሄደ ባለ ግምገማ ላይ በድንገት ፕሬዚዳንቱ ከዛሬ ዘጠኝ ኣመት በፊት ለተካሄደው ጭፍጨፋ ተጠያቂ መደረጉ የክልሉን ባለስልጣናትና የፖለቲካ አመራሮችን አስገርሟል ።

አስገምጋሚው ባለስልጣን "በጋምቤላ የተገደሉትን የአኙዋክ ጎሳዎች ስም ዝርዝር አዘጋጅተህ ያቀረብከው አንተ ነህ ትታሰራለህ" በማለት ሲናገሩ ግምገማው ላይ የተገኙ ባለስልጣናት የመደናገር ስሜት ታይቶባቸው ነበር። እኣአ 2003 በጅምላ ለተጨፈጨፉት የአኝዋክ ምሁራንና ንጹሃን ዜጎች ወንጀለኛ የተደረገው ፕሬዚዳንቱ የሰጠው መልስ ደግሞ ፍጹም ያልተጠበቀና አስደንጋጭ እንደሆነባቸው ምንጮቹ አስረድተዋል ተብሎአል።

"እኔ ከታሰርኩ ወታደርና መሳሪያ የሰጠኝ መለስም ይታሰራል" የሚል ድፍረት የተሞላበት ነገር ግን አለም ያወቀውን እውነት ለግምገማ በተላኩት የህወሃት ሹሞች ፊት ያለምንም ስጋትና ፍርሃት የተናገረው የጋምቤላ ፕሬዝዳንት ንግግር ያስገረመው ስሙ እንዳይገለጽ የጠየቀውና ከክልሉ ባለሥልጣኖች አንዱ መሆኑ በዘገባው የተጠቀሰው ምንጭ፤ "የህወሃት ታማኝ በመሆን የሚታወቀው ኦሞት ላይ እየተካሄደ ያለው ግምገማ መድረሻው እንደሚያጓጓው መናገሩን ጠቅሶአል።

ኦሞት ኦባንግ የጋምቤላ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከመሾሙ በፊት የወያኔዎች ካድሬ ማሰልጠኛ ከሆነው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ገብቶ እንደተማረ፣ ከዚያም የክልሉ የደህንነት ሐላፊ ሆኖ ማገልገሉና የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር በመሆን ለወያኔ ቅን አገልግሎት ያበረከተ እንደሆነ ይታወቃል።

ግለሰቡ ከህወሃት ጋር የነበረውን የጠበቀ ትስስር ለሶሊዳሪቲ ሙቭመንት ዘጋቢ የገለጹት ምንጮች እንደተናገሩት፤ በወያኔ የበላይ ሹሞች ትዕዛዝ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ሌላ ሰው ጭዳ ለማድረግ አሁን እንቅስቃሴ የተጀመረበት ምክንያት፤ መለስ በጋምቤላ የአኝዋክ ንጹሃን ላይ በተካሄደው ጭፍጨፋ ከፍተኛ አለም አቀፍ ውግዘት ስለደረሰበትና የዓለም አቀፉ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት (ICC)ና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጉዳዩን ለፍርድ ለማቅረብ መረጃዎችን ማጠናከሩን በመቀጠላቸው መለስ ዜናዊ በወቅቱ በዋንኛነት እንደመሳሪያ የተጠቀመበትን ሰው የወንጀሉ ተጠያቂ በማድረግ ከውንጀላው ነጻ ለመውጣት የነደፈው ስልት መሆኑን ያስረዳሉ።

በሌላም በኩል መለስ ክፉኛ እየተተቸበት ያለበትንና ገበናውን እያጋለጠው ያለው የመሬት ነጠቃ (land grabbing) የሚካሄደው በጋምቤላ በመሆኑ፣ የአገሬውን ተወላጅ በማፈናቀልና ለባርነት ተላልፈው እንዲሰጡ ማድረጉ በከፍተኛ ደረጃ ስሙንና አገዛዙን ስላጎደፈው፣ ለጎደፈው ስሙ ማደሻ የተገለገለበትን የጋምቤላ ሰው ኦሞትን እንደመስዋዕት በግ አሳልፎ በመስጠት ከተጥያቂነት ለማምለጥ መዘጋጀቱን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ይናገራሉ። መለስ ከህዝብ ጋር የገባበትን ቅራኔ በግለሰቦች ለማሳበብና ከደሙ ንጹህ ነኝ ለማለት ለጥፋት እንደመሳሪያ የተጠቀመባቸውን ሰዎች አሳልፎ መስጠት ወይም እንደአገዳ መጦ መጣል የተለመደ ታክቲኩ እንደሆነ ሁሉም አውቆታል።

ከዚህ በተጨማሪ በጋምቤላ ክልሉ ያለውን የደራ የመሬት ችብቸባ ገበያ ለመቀጠል በክልሉ አስተማማኝ ሰላም ስለሚያስፈልግ ፤ ካራቶሪ፣ ሳውዲ ስታርና ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ ለጀመሩት እርሻ ስጋት የሆኑ የአኝዋክ ወጣቶችን አባብሎ ከሸፈቱበት ጫካ እንዲወጡ ለማድረግ አቶ ኦሞትን የጅምላ ጭፍጨፋው ተጠያቂ ማድረግ ዋና ስልት ተደርጎ መወሰዱን የዜናው ምንጮች አስረድተዋል ። እንደዘና ዘገባው ምንጭ በዋናነት ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሳቢያ የአቶ ኦሞት ኦባንግ የስልጣን ዘመን ማክተሙን የሚናገሩት ለጉዳዩ ቅርብ የሆኑ ክፍሎች ለጋምቤላ ሰባተኛ ፕሬዚዳንት መዘጋጀቱን አመልክተዋል። ህወሃት ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ አራት ፕሬዚዳንቶች ግልጋሎታቸውን ካበረከቱ በሁዋላ ለእስር ሲዳረጉ አምስተኛው ፕሬዚዳንት የነበረው አቶ ኦኬሎ አኳይ ተሰደአል።

አቶ ኦኬሎ አኳይ የ2003ቱን የጅምላ ጭፍጨፋ አስመልክቶ ለሂዩማን ራይትስ ዎች የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጥ በአባይ ጸሃዬና ገብረአብ ባርናባስ ታዞ ነበር የሚለው ዘገባ ፕሬዚዳንቱ በወቅቱ ይፋ እንዳደረገው ግጭቱ የጎሳዎች የርስ በርስ እንደሆነ፣ አንድ ሰው ሲቆስል 59 ሰዎች መሞታቸውንና አንድ ቤት ብቻ መቃጠሉን ሪፖርት እንዲያደርግ ታዞ ባለመቀበሉ ህይወቱ አደጋ ላይ በመውደቁ ለመሰደድ ተገዶአል ብሎአል።

ከቀድሞ አለቃው መለስ ዜናዊ የጥቃት ስጋት የተሰነዘረበት ኦሞት ኦባንግ በተመሳሳይ ሊኮበልል ይችል እንደሆነ የሶሊዳሪቲ ዘጋቢ አስተያየት ሰጪዎችን ጠይቆ "አይሆንም። ጭፍጨፋውን አምልጠው ሱዳን ያሉ፣ በስደት ኬኒያ የገቡ የአኙዋክ ሰዎች አይፈቅዱለትም" የሚል ድፍን መልስ ማግኘቱን ዘግቦአል። ኦሞት ለወያኔ አለቆቹ ለሰራው ውለታ በ2005 ፕሬዚዳንት እንዲሆን መደረጉን የአኝዋክ ፍትሕ ምክርቤት (Anuak Justice Council) ጥቅምት 5፣ 2005 (እአአ) በድረ ገጹ ዘግቧል። ድረገጹ በዘገባው በጋምቤላ በተካሄደው ጭፍጨፋ እጁ እንዳለበት የተጠቆመው የፌደራል ደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣን አለማው አላምሩ መስከረም 25፣ 2005 ጋምቤላ በመሄድ "የመንግስትን ፖሊሲና እቅድ መተግበር የሚችል ብቸኛ ሰው ኦሞት ኦባንግ ነው" በማለት መናገሩን ገልጿል።

በመዠንገር፣ ኑዌርና አባል በሆኑበት የአኙዋክ ጎሳ ተቀባይነት እንደሌው የሚነገርለት ኦሞት ኦባንግ፣ ሰኔ 7፣ 2008 ካናዳ ከአኝዋክ ብሄረሰብ አባላት ጋር ሊያደርገው የነበረውን ውይይት የካናዳ መንግስት የመግቢያ ቪዛ ስለከለከለው ሳይሳካ መቅረቱን የካናዳ ድረገጽ (www.canada.com) በተመሳሳይ ቀን ዘግቦታል። በዘገባው የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ዳይሬክተር አቶ ኦባንግ ሜቶ "በሰብአዊ መብት ጥሰት የተወነጀለ ሰው ኢትዮጵያዊያንን ሰብስቦ የማነጋገር መብት የለውም" የሚል አስተያየት መስጠታቸውን አስፍሯል።

ግምገማው ሲጠናቀቅ ምን እንደሚወሰን የዜናው ምንጮች ግምት ከመስጠት ተቆጥበዋል ያለው የሶሊዳሪቲ ዘገባ ስለጉዳዩ ያነጋገራቸው አቶ ኦባንግ ሜቶ ግን "ኦሞትን በተመለከተ እየተካሄደ ስላለው ግምገማ በቂ መረጃ አለን። በግፍ ለተጨፈጨፉት የአኝዋክ ንጹሃን ዜጎች የፍርድ ሂደት ጠቃሚ ግብአቶች አግኝተናል። የቀን ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መለስም ሆነ ሌሎች በድርጊቱ የተሳተፉ ለፍርድ ይቀርባሉ። ኢትዮጵያም ፍትህ ታገኛለች" በማለት በእጃቸው ስለገባው መረጃ በዝርዝር ከመናገር ተቆጥበዋል ብሎአል።

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ በሽብርተኝነት የ11 አመት እስር

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ጋዜጠኞችን ለመፍታት ያለው ብቸኛ አማራጭ ይቅርታ መጠየቅ ነው የሚሉት የስዊድን ባለስልጣናት፣ ይህ ማለት ግን ጋዜጠኞች ጥፋተኛ ናቸው ማለት አለመሆኑን ገልጠዋል።

ጋዜጠኞች ጥፋተኞች ነን ብለው ካላመኑ እንዴት ይቅርታ ሊጠይቁ እንደሚችሉ የተገለጠ ነገር ባይኖርም በበታቾችነት ስሜት የሚሰቃዬው መለስ ዜናዊ ጠላቶቼ ናቸው በሚላቸው ላይ የበላይነቱን ለማሳየት ያለምንም በቂ ማስረጃ አስሮ ይቅርታ እንዲጠይቁ ማድረግ ልማዱ እንደሆነ የሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን ስለ ሁኔታው አልተገረሙም።

ግንቦት 7 በሁለቱ ጋዜጠኞች ላይ የተሰጠውን የፍርድ ውሳኔ በመቃወም መግለጫ ባወጣበት ወቅት መለስ ዜናዊ ውሎ ሳያድር ከአለም አቀፍ ህብረተሰብ የሚደርስበትን ውግዘት ለመገላገል ይቅርታ አስጠይቆ እንደሚለቃቸው ተንብዮ እንደነበር አይዘነጋም።

መለስ ዜናዊና የወያኔ ሹመኞች ሁለቱን የሲዊድን ጋዜጠኞች በማሰር ያተረፉት ነገር ቢኖር ዜጎቻችንን በምን አይነት እስር ቤት ውስጥ አስረው እንደሚያሰቃዩ የአለም ህዝብ እንዲያውቅ ማድረግን ብቻ እንደሆነ የምናገረው ዘጋቢያችን ካሪን ሸበየ ለ ሲ ኤን ኤን በሰጡት ቃል 250 የሚደርሱ እስረኞች በአንድ ክፍል ውስጥ እንደሚታሰሩና መኝታ ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ እስረኞች እንደሚሰቃዩ ከሰለባዎቹ ስዊድናዊያን ማረጋገጣቸውን መናገራቸው በቂ ማስረጃ ነው ብሎአል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org